# በኢትዮጵያ አጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የዐማርኛ ቋንቋ ፈተና የቅደምተከተል (sequencing) አስተካክል ጥያቄ ግምገማ

ማረው ዓለሙ[1]


## አሕጽሮተጥናት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ ኹለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ የዐማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎችን መገምገም ነው፡፡ የጥናቱ የመረጃ ምንጮች ከ1998-2004 ዓ.ም. የሰባት ዓመት የዐማርኛ ቋንቋ ፈተና ጥራዞች ናቸው፡፡ በኹሉም ጥራዞች የተገኙት ስምንት የቅደምተከተል አስተካክል ናሙና ጥያቄዎች የጥናቱ መረጃዎች ናቸው፡፡ ጥናቱ የተከናወነው በግምገማ ስልት ሲሆን፣ የግምገማ ትኩረቶችም በቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄና በሚለካው የቋንቋ ችሎታ፣ በቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄና በሚያስገኘው ነጥብ መካከል ያለው መጣጣም፣ የመነሻ መልስና ለከፊል መልስ ከፊል ውጤት፣ የቅደምተከተል አመላካች አካላትና የጥያቄዎች ነፃነት ናቸው፡፡ የመተንተኛ አሐዱም የዓረፍተነገሮች ቅደምተከተል ነው፡፡ እንዲሁም በሙያው የሚሠሩ ሦስት የዩኒቨርሲቲ መምህራን ለጥያቄዎቹ በየግላቸው ያዘጋጁቸው መልሶች ለግምገማው በግብዓትነት አገልግለዋል፡፡ በውጤት ትንተናው መሠረትም በቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄና በሚለካው የቋንቋ ችሎታ መካከል መጣጣም አልታየም፤ ቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ እንዲለካ የሚጠበቀው የማንበብ ክሂል ችሎታን ቢሆንም፣ በዚህ ጥናት የመረጃ ምንጮች ግን ጥያቄው የቀረበው የመጻፍ ክሂል ችሎታን እንዲለካ ታስቦ መሆኑን ከውጤት ትንተናው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለዚህም ሲባል በአንድ ቅደምተከተል አስተካከል ጥያቄ መሠረት መረጃው ከሚችለው በላይ በቀረቡት ጥያቄዎች መካከል መደጋገፍ ወይም የመረጃ ተጋቦት ታይቷል፡፡ ይህም የጥያቄዎችን ራስን ችሎ አንድን የቋንቋ ችሎታ ዘርፍ የመለካት ብቃት እንደጎዳው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ የውጤት ትንተናው እንዳመላከተው ኹሉም የጥናቱ ናሙና ጥያቄዎች በመልስ አስመራጭ ቅርፅ የቀረቡ ኾነው፣ ቢያንስ አንድ መነሻ መልስ ግን የላቸውም፡፡ ይህም በዓረፍተነገሮቹ ከተገቢ የቅደምተከተል አመላካቾች ጉድለት ጋራ ተዳምሮ ጥያቄዎቹን አወሳስቧቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ የሚጠበቀው መሉ መልስ በመኾኑ በዚህ ረገድ የነጥብ አሰጣጡ የፍትሐዊነት ችግር እንዳለበት የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ በጥናቱ ውጤት መሠረትም ከቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ ጋራ በተያያዘ የሚከሰቱትን ችግሮች በመጠኑም ቢሆን ለመቀነስ እንዲቻል መፍተሄዎች ተጠቁመዋል፡፡


## መግቢያ

የማንበብ ተግባር በባሕርይው ውስብስብ ነው፡፡ በዚህም አስፈላጊ ከሚባሉት ችሎታዎች መካከል አንደኛው በቴክስት ውስጥ የሐሳብ አደረጃጀትን ወይም የሐሳብ መዋቅር መረዳትን ይመለከታል፡፡ አንብቦ መረዳትን በመፈተን ሂደት የተለያዩ የጥያቄ ቅርፆች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ እንደብራውን (2004) አገላለፅ፣ የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ አንደኛው ነው፡፡ ጥያቄው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከሚለካባቸው መንገዶች አንደኛው ነው፡፡ የታሪክን ቀድምተከተል ወይም የአንድን ድርጊት የአፈፃፀም ሂደት መሠረት አድርጎ ሊቀርብ ይችላል፡፡ የጥያቄው ተቀዳሚ ዓላማ የመላውን ታሪክ፣ አንቀጽ፣ ድርሰት ወዘተ. ሐሳብ ወይም መልዕክት በትክክል መረዳትን መፈተሽ ነው፡፡ ለዚህም የቅደምተከተል አመልካች አካላት (አያያዦች) ያስፈልጋሉ፡፡ አንድ ሐሳብ ሌላውን አስቀድሞና ሌላውን ደግሞ አስከትሎ ስለመደራጀቱ በማሳየት ረገድ ቅደምተከተል አመልካቾች ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ ኦልደርሰንና ሌሎች (2000) እና ኦልደርሰንና

1 . Ethiopian Languages and Literature-Amharic Department, Bahir Dar University, Bahir Dar, Ethiopia

*Corresponding author: marewalemu@gmail.com*

ሌሎች (1995) እንደሚገልፁት በቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ ተፈታኞች የሐሳብ ቅድምተከተላቸው የተፋለሰ ዓረፍተነገሮችን በትክክለኛ ቦታቸው በማሰለፍ አንድ ተጠየቃዊ የሐሳብ መዋቅር እንዲፈጥሩ ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡ ይህም ለብዙ ተፈታኞች ቀላል አይሆንም፤ በአንድ ብቸኛና ትክክለኛ መዋቅር ብቻ ዓረፍተነገሮችን ማደራጀት ውስብስብና ጊዜ ጠያቂ ተግባር ሊሆን እንደሚችል መገመት አያስቸግርም፡፡ እንደአልደርሰንና ሌሎች አገላለፅ፣ ችግሩ በተፈታኞች ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን ለፈተና አራሚዎችም ይደርሳል፡፡ በተለይም ፈተናው ለከፊል መልስ፣ ከፊል ነጥብ የሚፈቅድ ሲሆን ሁኔታው ይበልጥ ሊወሳሰብ ይችላል፡፡

ለቅድምተከተል አስተካክል ጥያቄ ዝግጅት ቴክስቶች የሚመረጡት ለአንድ ለተወሰነ ዓላማ በአንድ የተወሰነ የሐሳብ አደረጃጀት ከተጻፉ ጽሑፎች ነው፡፡ አልደርሰንና ሌሎች (2000) እንደሚያስረዱት ግን የእንደነዚህ ዓይነት ጽሑፎች ጸሓፊዎች ለራሳቸው ዓላማ ብቻ ስኬት በማሰብ የሐሳቦችን ቅደምተከተል አመልካች አካላት ወይም አያያዦች በግልፅ ማሳየት ላያስፈልጋቸው ይችላል፡፡ ምክንያቱም ለሚፈለገው ዓላማ ሐሳቡ በአንድ ዓይነት ተዋረድ እስከተደራጀ ድረስ ጸሓፊዎቹ ቅደምተከተል አመልካቾችን በግልፅ እንዲያሳዩ የግድ ላይሆን ስለሚችል ነው፡፡ እነዚህ ቴክስቶችም ግልፅ የሆነ ቅደምተከተል አመልካቾች ሳይኖራቸው ዓረፍተነገሮቹ ቅደምተከተላቸው ተዘበራርቆ ወይም ተፋልሶ ተፈታኞች እንዲያስተካክሏቸው በሚጠየቁበት ጊዜ ፈታኝ መሆናቸው አይቀርም፡፡ የዚህም ምክንያቱ የቅደምተከተል አመላካች አካላት ሳይኖራቸው ዓረፍተነገሮቹ ቅደምተከተላቸው ከተፋለሰ መልሶ በተገቢው ቅደምተከተል የማደራጃ ግልፅ የሆነ ውል ስለማይኖራቸው ነው (አልደርሰንና ሌሎች፣ 2000)፡፡ በዚህም የተነሳ የፈተና አዘጋጆች ዓረፍተነገሮቹን በአንድ ብቸኛ ስሜት ሰጭ ተዋረድ ወይም ቅደምተከተል ለማደራጀት የግድ የሚያደርጉ ተገቢ የግጥምጥሜ አካላትን ወይም አያያዦችን በተገቢ ቦታቸው በማካተት ቴክስቱን እንደገና ማሻሻል ይጠበቅባቸው ይሆናል፡፡ እንዲህም ኾኖ የጥያቄውን ውስብስብነት ከግምት በማስገባት ከአንድ ወይም ከኹለት መነሻ መልስ ጋራ ማቅረብ አንድ አማራጭ ሊሆን ይችላል (ሂተን፣ 1990፤ ሂዩዝ 2003)፡፡ በተለይም በዓረፍተነገሮች ትክክለኛ ቅደምተከተል መሠረት ተፈታኞች የመጀመሪያው ዓረፍተነገር ትክክለኛ ቦታ ከተነገራቸው ከእሱ በመነሳት ቀሪዎቹን በትክክለኛ ቅደምተከተላቸው ለማሰለፍ ብዙ ላይቸገሩ ይችላሉ፡፡ ይህ አሠራር አሻሚነትን በመቀነስ ረገድም የራሱ ሚና አለው፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ግን ተፈታኞቹ ምንም ዓይነት መነሻ መልስ ወይም ፍንጭ ሳይሰጣቸው ኹሉንም ቅደምተከተላቸው የተፋለሰ ዓረፍተነገሮች እንዲያደራጁ የሚጠየቁ ከኾነ የአንድ ወይም የኹለት ስሕተት ለሌሎች ተጨማሪ ስሕተቶች ሊዳርጋቸው ይችላል (ሂተን፣ 1990)፡፡ ተፈታኞች ለምሳሌ፣ በኹለት ወይም በሦስት የተሳሳቱ የዓረፍተነገሮች ቅደምተከተሎች ከጀመሩ ቀሪዎቹን ዓረፍተነገሮች በትክክለኛው ተዋረድ ለማደራጀት ይቸገራሉ፡፡ የዚህም ምክንያቱ ከላይ እንደተገለፀው በጥያቄው ባሕርይ የተነሳ አንድ ስሕተት ለሌላ ተጨማሪ ስሕተት ስለሚዳርግ ነው፡፡ ይህም ማለት አንደኛው ስሕተት ለሌላኛው ስሕተት እያቀበለ ስሕተቶቹ እየተወላለዱና እየበዙ ይሄዳሉ ማለት ነው፡፡ ይህም ችግር፣ ሂተን እንደሚያስረዱት፣ በፈተናው እርማትና ነጥብ አሰጣጥ ላይም በግልፅ ይንፀባረቃል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በስሕተቶች መወላለድ የተነሳ አንድ ስሕተት ቢያንስ ኹለት ነጥብ ሊያሳጣ ይችላል፡፡ አንድ ዓረፍተነገር የትክክለኛ ቅደምተከተል ቦታውን ስቶ ያለቦታው በመገኘቱም፣ አንደኛ የራሱን ትክክለኛ ቦታ ባለመያዙ አንድ ነጥብ ሲያሳጣ፣ ኹለተኛ የራሱን ቦታ መሳቱ ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ዓረፍተነገር ቦታ በመያዙ ሌላ አንድ ነጥብ ያሳጣል ማለት ነው፡፡

የቅድምተከትል አስተካክል ጥያቄ አንደኛው ድክመቱ አንድ ብቸኛ ቅድመተከተልና ትክክለኛ ሙሉ መልስ የግድ ማድረጉ ነው (አልደርሰንና ሌሎች፣ 1995፤ አልደርሰንና ሌሎች፣ 2000፤ ብራውን፣ 2004፤ ሂተን፣ 1990፤ ሂዩዝ፣ 2003)፡፡ ጥያቄው ለአማራጭ ቅድምተከተልና ለከፊል መልስ እድል አይሰጥም፡፡ አንድ ታሪክ ወይም ሐሳብ በአንድ ዓይነት ቅደምተከተል ብቻ እንዲደራጅ የግድ የሚያደርግ ተጠየቅ ባለመኖሩ በዚህ ረገድ ቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ

ድከመት አለበት፤ ቢባል ምክንያታዊ ይመስላል፡፡ ለምሳሌ፣ ቅደምተከተላቸው የተፋለሰው ስድስት ዓረፍተነገሮች [ሐ፣ ሠ፣ ሀ፣ ረ፣ መ፣ ለ] ሙሉ ውጤት/ነጥብ የሚያሰጠው ትክክለኛ ቅደምተከተላቸው [መ፣ ለ፣ ረ፣ ሐ፣ ሠ፣ ሀ] ቢሆን ከዚህ ያፈነገጠ ማንኛውም ቅደምተከተል በከፊል ትክክል ቢሆንም ውጤት አያስገኝም፡፡ እንበል የአንድ ተፈታኝ መልስ [መ፣ ለ፣ ሐ፣ ረ፣ ሀ፣ ሠ] ቢሆን (በከፊልም ቢሆን የመጀመሪያዎቹ የኹለቱ ጥንድ ዓረፍተነገሮች ቅደምተከተል ትክክል ኾኖ እያለ) ምንም ውጤት አይመዘገብለትም ማለት ነው፡፡ አልደርሰንና ሌሎች (1995) እንደገለፁት፣ በቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ አንድ ብቸኛ ቅደምተከተል የሚጠበቅና ይህም የሚያስገኘው አንድ ነጥብ ብቻ በመሆኑ፣ ሙሉ በሙሉ በተሳሳቱና በከፊል ሙከራ ያደረጉ (አንድ ወይም ኹለት ስሕተት ያላቸውም ቢሆኑ) ተፈታኞች ኹለቱም ምንም ውጤት አይመዘገብላቸውም፡፡ ይህም የፍትሐዊነት ችግር ያለበት ስለመኾኑ መገመት አያስቸግርም፤ ለሙሉ ትክክለኛ ቅድመተከተል ብቻ አንድ ነጥብ ብቻ መስጠት፣ ተፈታኞች ወደትክክለኛው መልስ ለመድረስ የሚያደርጉትን ከፍተኛ ጥረት ኹሉ ዋጋ ማሳጣቱ አሠራሩን ፍትሐዊ አያደርገውም፡፡ ስለዚህም ቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ እጅግ ውስብስብና ሰፊ ጊዜ የሚጠይቅ ኾኖ እያለ ለአንድ ትክክለኛ ቅደምተከተል ብቻ አንድ ነጥብ ብቻ እንዲሰጥ መደረጉ የውጤት አሰጣጡን ኢፍትሐዊነት በግልፅ ያመላክታል (አልደርሰንና ሌሎች፣ 2000)፡፡

እንደአልደርሰንና ሌሎች አገላለፅ፣ ይህንንም ችግር ለመፍታት የሚያስችለው አንዱ አማራጭ ማንኛውም ዓረፍተነገር ትክክለኛ ቦታውን ይዞ ከተገኘ ከፊት ወይም ከኋላ ያለው ዓረፍተነገር ስሕተት ቢሆንም ለአንድ ነጠላ ቅደምተከተል ትክክለኛ መልስ 1 ነጥብ መመዝገብ ነው፡፡ ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሠረት የቀሪዎቹ አራት ዓረፍተነገሮች ቅደምተከተል ስሕተት ሆኖ (ሐ) በአራተኛ ደረጃ ትክክለኛ ቦታውን ይዞ ቢገኝ 1 ነጥብ ይመዘገብለታል ማለት ነው፡፡ ይህም ቅንፉ ትክክለኛ መልስ መሆኑን በማመላከት [ለ፣ ረ፣ መ (ሐ)፣ ሀ፣ ሠ] በሚል ሊገለፅ ይችላል፡፡ በዚህ ዓይነት በሠንጠረዥ 1 እንደሚታየው 30 ዓይነት የቢሆን ወይም ሰውሠራሽ ቅደምተከተል በመፍጠር በውስጡ ያሉትን ተናጠላዊ መልሶች ማስተዋል ይቻላል፡፡

**ሠንጠረዥ 1**፤ *የትክክለኛ ቦታ ቅደምተከተል (መ፣ ለ፣ ረ፣ ሐ፣ ሠ፣ ሀ) መፋለስ*

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ረ | ሀ | ለ | መ | ሐ | ሠ |
| ሠ | ረ | ሀ | ለ | መ | ሐ |
| ሐ | ሠ | **(ረ)** | ሀ | ለ | መ |
| **(መ)** | ሐ | ሠ | ረ | ሀ | ለ |
| ለ | መ | ሐ | ሠ | ረ | (ሀ) |

በሰንጠረዥ 1 የተመለከቱት ዐምስት ቅደምተከተሎች (በረድፍ ማለት ነው፡፡) ተገማች ሲሆኑ፣ ከዐምስቱ ቅደምተከተሎች ሦስቱ በከፊልም ቢሆን አንድ የትክክለኛ ቦታ ቅደምተከተል (exact match) መልስ አላቸው፡፡ ኾኖም የአንድ ብቸኛ ቅደምተከተል ትክክለኛ ሙሉ መልስን የግድ በሚያደርግ አፈታተን ለእንደነዚህ ዓይነቶቹ ከፊል ትክክለኛ መልስ ምንም ነጥብ ማግኘት አይቻልም፡፡

በዚህም ብቸኛ የትክክለኛ ቅደምተከተል መልስ በራሱ ድክመቶች እንዳሉት መረዳት ይቻላል፡፡ በከፊልም ቢኾን የሐሳብ ክትትሎሽን ከግምት አለማስገባት ከአንብቦ መረዳት መርህ ጋራ የሚጣጣም አይኾንም፤ አንደኛው ሐሳብ ሌላውን ተከትሎ ሲመጣ ወይም አንደኛው ሐሳብ ሌላውን ቀድሞ ሲገኝ በመካከላቸው ያለውን ምክንያታዊ ግንኙነት መረዳት የሚያስችል

ክትትሎሽ ሲኖር በከፊልም ቢሆን አንብቦ መረዳትን ሊያመላክት ይችላል፡፡ በመሆኑም ኦልደርሰንና ሌሎች (2000) እንደገለፁት፣ የነጠላ ትክክለኛ መልስ ቢያንስ በጥንድ ዓረፍተነገሮች ደረጃ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ስለማያመላክት ፍትሐዊነቱ ግርድፍ ነው፤ ለማለት ይቻላል፡፡ ስለኾነም ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው በተለይም ተገቢ ቅደምተከተል የሌላቸው ዓረፍተነገሮች ቦታቸው ተፋልሶ ተፈታኞች እንዲያስተካክሉ በሚጠየቁበት ጊዜ ከተግባሩ ውስብስብነት የተነሳ አንድ ብቸኛና ትክክለኛ ቅደምተከትል መፍጠር ስለሚሳናቸው ለከፊል የሐሳቦች ቅደምተከተል ግንዛቤ ወይም መረዳት ዋጋ መስጠት ምክንያታዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ኾኖም ይህ በራሱ ደግሞ የጥያቄውን አስተራረምና ውጤት አመዘጋገብ እያወሳሰበው ስለሚሄድ ልኬታው ለአስተማማኝነት ችግር ሊጋለጥ ይችላል፡፡

በኦልደርሰንና ሌሎች (2000) እንደተጠቆመው፣ ለዚህ ዓይነቱ ውስብስብ አስተራረምና የውጤት አሰጣጥ ችግር አንደኛው አማራጭ መፍትሄ መስጫ ዘዴ ዓረፍተነገሮችን በጥንድ ወይም በመንትዮሽ ማረምና ክትትላቸው ትክክል ሆኖ ሲገኝ 1 ነጥብ መመዘገብ ነው፡፡ እንበል ቅደምተከተላቸው የተፋለሰው ዐምስት ዓረፍተነገሮች በዚህ [ለ፣ መ፣ ሀ፣ ሠ፣ ሐ] ቅደምተከተላቸው ኹሉም ትክክለኛ ቦታቸውን ይዘው ሲገኙ፣ ተፈታኙ 4 ነጥብ ሊመዘገብለት ይችላል፡፡ በዚህም "ለ"ን አስቀድሞ ሲገኝ ለ"መ" 1 ነጥብ፣ "መ"ን አስቀድሞ ሲገኝ ለ"ሀ" 1 ነጥብ፣ "ሀ"ን አስቀድሞ ሲገኝ  ለ"ሠ" 1 ነጥብና "ሠ"ን አስቀድሞ ሲገኝ ለ"ሐ" 1 ነጥብ በመመዝገብ ይከናወናል፡፡ ከዚህ ውጭ ሲሆን ደግሞ የጥንድ ዓረፍተነገሮችን ክትትሎሽ መሠረት በማድረግ ጥንድ ዓረፍተነገሮች ትክክለኛ ቦታቸውን ይዘው ሲገኙ 1 ነጥብ መመዝገብ ሌላ አማራጭ ይሆናል፡፡ ይህም የሚሆነው "ለ"ን ሲያስቀድም ለ"መ" 1 ነጥብ፣ "መ"ን ሲያስቀድም ለ"ሀ" 1 ነጥብ፣ "ሀ"ን ሲያስቀድም ለ"ሠ" 1 ነጥብ፣ "ሠ"ን ሲያስቀድም ለ"ሐ" 1 ነጥብ ወዘተ. በሚል መርህ ለትክክለኛ ጥንድ ዓረፍተነገሮች ክትትሎሽ ውጤት በመመዝገብ ነው፡፡ ይህም ውስብስብ ባለመሆኑ ኢጋዥ የኮምፒዩተር ፕሮግራምን መጠቀም ሳይጠይቅ በሰው ብቻ ሊከናወን ይችላል፡፡ ለተጨማሪ አስረጂ እንዲሆን ተገማች የጥንድ ዓረፍተነገሮችን ቅደምተከተል በቢሆን ወይም ሰውሠራሽ በሆነ መልኩ በሠንጠረዥ 2 ማየት ይቻላል፤

**ሠንጠረዥ 2**፤ *የጥንድ ቅደምተከትል መፋለስ*

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ለ | X | ሐ | መ | X | ሠ | ረ |
| X | ሀ | ለ | X | ሐ | መ | X | X |
| X | X | ሀ | ለ | X | ሐ | መ | X |
| ሠ | ረ | X | ሀ | ለ | X | ሐ | መ |
| X | ሠ | ረ | X | ሀ | ለ | X | X |

በሠንጠረዥ 2 በመጀመሪያው ረድፍ በብቸኛ ቅደምተከተል ሙሉ መልስ መርህ መሠረት የኹለቱ ጥንድ ዓረፍተነገሮች [ሀለ] ቅደምተከተል ትክክለኛ መልስ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ኹሉም ጥንድ ዓረፍተነገሮች ግን ክትትላቸው ትክክል ቢሆንም ትክክለኛ ቦታቸውን ስለሳቱ እንደትክክለኛ መልስ አይቆጠሩም፤ ውጤትም አይመዘገብላቸውም፡፡ ይህም በራሱ ግን የጥንድ ዓረፍተነገሮችን ክትትሎሽ በትክክል ማሳየት መቻል በከፊልም ቢሆን ቴክስቱንና የሐሳቡን ተዋረድ መረዳትን ስለሚያመላክት ዋጋ ሊያስገኝ ይገባል፤ በሚል ሊያከራክር ይችላል፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ከፊል ግንዛቤ ዋጋ አለመስጠትም ለተፈታኞች ሙሉ ጥረትና ችሎታ ፍትሕን መንፈግ ሊሆን ይችላል፡፡

ቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ ከጥንድ ዓረፍተነገሮች ቅደምተከተል በላይም ቢሆን ወደሙሉው መልስ በሚቃረብ መልኩ ቴክስቱን ለመረዳት ጥረት ላደረጉ ተፈታኞች ዋጋ አይሰጥም፡፡ በአልደርሰንና ሌሎች (2000) እንደተገለፀው ለምሳሌ፣ አንድ ተፈታኝ ከጥንድ ወይም ከመንትዮሽ ዓረፍተነገሮች በላይ የሦስትዮሽ ዓረፍተነገሮች ትክክለኛ ቅደምተከተል መልስ ቢኖረው እንዴት ነው ውጤት የሚመዘገብለት? ለሚለው ጥያቄ መልስ የለውም፡፡ በአንድ ብቸኛ ቅደምተከተል ሙሉ መልስ የሦስቱ ዓረፍተነገሮች ከትትል ትክክል ኾኖ ቦታቸው ሲፋለስ ምንም ዓይነት ውጤት እንደማያስገኝ በሠንጠረዥ 3 የቀረቡት ተገማች ቅደምተከተሎች አስረጂ ይኾናሉ፡፡

***ሠንጠረዥ* 3**፤ *የሦስትዮሽ ጥንድ መፋለስ*

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| *ሀ* | *ለ* | *ሐ* | X | *መ* | *ሠ* | *ረ* | X |
| X | *ሀ* | *ለ* | *ሐ* | X | *መ* | *ሠ* | *ረ* |
| X | X | *ሀ* | *ለ* | *ሐ* | X | X | X |
| X | X | X | *ሀ* | *ለ* | *ሐ* | X | X |
| *መ* | *ሠ* | *ረ* | X | *ሀ* | *ለ* | *ሐ* | X |

በሠንጠረዥ 3 በመጀመሪያው ረድፍ እንደተመለከተው በሦስትዮሽ ቅደምተከተል እንደትክክለኛ መልስ የሚቆጠሩት [ሀለሐ] ብቻ ናቸው፡፡ በዚሁ ረድፍ ቀሪዎቹን ጨምሮ በኹለተኛው፣ በሦስተኛው፣ በአራተኛውና በዐምስተኛው ረድፎች ያሉት ኹሉም ምላሾች ተፈታኙ ስለሐሳቦች ውስጣዊ መተሳሰር ስላለው ግንዛቤ መረጃ የሚሰጡ ቢኾኑም፣ ስሕተት ናቸው፡፡ ነገርግን እንደነዚህ ዓይነት መልሶች ከጥንድ ዓረፍተነገሮች ትክክለኛ ቅደምተከተል የበለጠ፣ ከሙሉው መልስ ያነሰ ዋጋ ሊሰጣቸው አይገባም? በሚልም ለሚነሳው ተጠየቃዊ ጥያቄ ቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ ተገቢ መልስ የለውም፡፡ በዚህ ረገድ ከጥንድ ዓረፍተነገሮች ቅደምተከተል በላይ ለበርካታ ዓረፍተነገሮች ቅደምተከተሎች ዋጋ መስጠት ምክንያታዊ ቢሆንም፣ ይህም በራሱ አስተራረሙንና የነጥብ አሰጣጡን በከፍተኛ ደረጃ ሊያወሳስበውና ለአስተማማኝነት ችግር ሊያጋልጠው ይችላል (አልደርሰንና ሌሎች፣ 2000)፡፡ በርግጥ እያንዳንዱ ዓረፍተነገር ከሌላው ነፃ ኾኖ ራሱን ችሎ የሚታረም ቢኾን ከሠንጠረዥ 1 እስከሠንጠረዥ 3 የቀረቡት አስረጂ ናሙናዎች አንዳች ዋጋ ሊሰጣቸው እንደሚችል ልብ ማለት ይገባል፡፡ አልደርሰንና ሌሎች እንደሚያስረዱትም፣ ተፈታኞች የተወሰኑ ዓረፍተነገሮች ትክክለኛ ቦታቸውን በሳተ ኹኔታ በትክክለኛ ቅደምተከተላቸው አደራጅተው እያለ ይህን ኹሉ ጥረታቸውን ዋጋ ማሳጣት ፍትሐዊ አይሆንም፡፡ ስለዚህም በቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ ለከፊል መልስ ዋጋ ማስገኘት የሚያስችል አንዳች ብልሃት መቀየስ አስፈላጊ ነው፤ ቢባል ምክንያታዊ ሊሆን ይችላል፡፡

የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ የማንበብ ችሎታን የተወሰነ ዘርፍ በትክክል የመለካት ብቃት እንዳለው ተቀባይነት እንዳለው ከታወቀ ስለቅደምተከተሉ አስተራረምና ነጥብ አሰጣጥ በውል ማሰብ ያስፈልጋል (አልደርሰንና ሌሎች፣ 2000)፡፡ ከላይ በግልፅ ለማሳየት እንደተሞከረው የትክክለኛ ቦታ ቅደምተከተል በከፊል ትክክለኛና ሙሉ በሙሉ ስሕተት በሆኑ ቅደምተከተሎች መካከል ያለውን ልዩነት ካሳየም በጣም በትንሹ ስለሆነ ግርድፍ እንጂ ብዙም የጠራ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ በተጨማሪም፣ በቅደምተከተሉ ከትክክለኛ ቦታቸው ውጭ የአላባዉያንን

ክትትሎሽ ከግምት አያስገባም፡፡ ይህንንም ችግር ለማስወገድ እንዲቻል ኦልደርሰንና ሌሎች እንዳመላከተቱት፣ ቅደምተከተል በራሱ በቴክስት ክፍሎች የርስበርስ ተዛምዶ (ትስስር) ላይ የሚመሠረት ስለሆነ፣ ለተጨማሪ አማራጭ ከዚሁ እሙን መነሳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም፣ የመጀመሪያውን ቅደምተከተል መለየት መቻል በሌሎች አላባዊያን መካከል ያለውን ዝምድና ለመለየት እንደቅድመሁኔታ ሊወሰድ አይችልም፤ ቢባል ተጠየቃዊ ይመስላል፡፡ በሌላ አባባል በቅደምተከተሉ ማንኛውም አላባ ትክክለኛ ቦታውን ቢስት፣ ይህ አላባ ሌሎች አላባዊያን ርስበርስ ተሳስረው ለሚፈጥሩት ትክክለኛ ቅደምተከተል መነሻ ሊሆን ይችላል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን እሙኖች መሠረት በማድረግም ኦልደርሰንና ሌሎች (2000) የሦስትዮሽ የነጥብ አሰጣጥ (triplet scoring) ሕግ (algorithm) አስተዋውቀዋል፡፡ በሦስትዮሽ የነጥብ አሰጣጥ ሕግ መሠረትም በቅደምተከተሉ ለማንኛውም አላባ (element) ከፍተኛው ነጥብ ሦስት ነው፡፡ በዚህም ለትክክለኛ ቦታ ቅደምተከተል 1 ነጥብ ይሰጣል፤ ኹለተኛው ነጥብ በቅደምተከተሉ ትክክለኛ አላባ ላስቀደመ አላባ ይሰጣል፤ ከዚህ ላይ ግን አላባው በቅደምተከተሉ መነሻ ወይም የመጀመሪያ ከኾነና ዳረኛ (edge) በመሆኑ ትክክለኛ አላባ ሊያስቀድም ስለማይችል፣ ኹለተኛው ነጥብ ይመዘገብለታል፤ ማለት ነው፡፡ ሦስተኛው ነጥብ ደግሞ በቅደምተከተሉ ትክክለኛ አላባ ላስከተለ አላባ ይሰጣል፡፡ ከዚህም ላይ እንደመነሻው አላባ ኹሉ በቅደምተከተሉ ለመድረሻ ወይም ለመጨረሻ አላባ ብቻ (ዳረኛ ስለኾነና ትክክለኛ አላባ ሊያስከትል ስለማይችል) 1 ነጥብ ይሰጣል፡፡ በዚህም መሠረት ሦስትዮሽ የውጤት አሰጣጥ በአላባዊያን መካከል ያለውን የርስበርስ መተሳሰር ከመገንዘብ አንፃር እንደአንብቦ የመረዳት መለኪያ አሐድ ሊቆጠር ይችላል፡፡ ከውጤት አሰጣጥ ዘዴው መረዳት እንደሚቻለው የሦስትዮሽ የውጤት አሰጣጥ ሕግ ለትክክለኛ ሦስትዮሽ ቅደምተከተል ብቻ ውጤት መስጠትን ወይም የቴክስቱን ሦስትዮሽ ቅደምተከተል መፍጠርን አያመላክትም፡፡ ከዚህ ይልቅ የቴክስቱ አላባዊያን ተጠየቃዊ ቅደምተከተል መፍጠር በዓረፍተነገሮች መካከል የርስበርስ ትስስር እንደመመሥረት ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ በሦስትዮሽ የውጤት አሰጣጥ ሕግ ማሕቀፍ መሠረት ተጠየቃዊ ተዛምዶ፣ አንዱ ሐሳብ ሌላውን አስቀድሞና ሌላውን አስከትሎ የሦስትዮሽን መተሳሰር ይመለከታል፡፡

የሦስትዮሽ ሕግ ኹለት ጠቀሜታዎች አሉት፤ የውጤት አሰጣጡ ኹለቱንም ፍትሐዊነትንና በተፈታኞች መካከል ያለ ልዩነትን በተሻለ ሁኔታ ማረጋገጥ መቻሉ አንደኛው ጠቀሜታው ሲሆን፣ ኹለተኛው ደግሞ ቅደምተከተል አስተካክል ተግባራትን እንዲሁም ምላሾቻቸውን ለመተንተንና ለመተርጎም የሚያስችል ፅንሰሐሳባዊ ማሕቀፍ መያዙ ነው (ኦልደርሰንና ሌሎች፣ 2000)፡፡

**ሠንጠረዥ 4**፤ *የቅደምተከተል ተግባራት ነጥብ (ውጤት)*

| የትክክለኛ ቅደምተከተሎች መፋለስ | | | | | | | | *የነጥብ አሰጣጥ ዘዴ* | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | ትክክለኛ | ቀዳሚ | ተከታይ | ዳረኛ |
| ሸ | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ | ሰ | 0 | 6 | 6 | 0 |
| ሰ | ሸ | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ | 0 | 6 | 6 | 0 |
| ረ | ሰ | ሸ | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | 0 | 6 | 6 | 0 |
| ሠ | ረ | ሰ | ሸ | ሀ | ለ | ሐ | መ | 0 | 6 | 6 | 0 |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መ | ሠ | ረ | ሰ | ሸ | ሀ | ለ | ሐ | 0 | 6 | 6 | 0 |
| ሐ | መ | ሠ | ረ | ሰ | ሸ | ሀ | ለ | 0 | 6 | 6 | 0 |
| ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ | ሰ | ሸ | ሀ | 0 | 6 | 6 | 0 |

የጥንዶሽ መፋለስ

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ለ | X | ሐ | መ | X | ሠ | ረ | 2 | 3 | 3 | 1 |
| X | ሀ | ለ | X | ሐ | መ | X | X | 0 | 2 | 2 | 0 |
| X | X | ሀ | ለ | X | ሐ | መ | X | 0 | 2 | 2 | 0 |
| X | ረ | X | ሀ | ለ | X | ሐ | መ | 0 | 3 | 3 | 0 |
| X | ሠ | ረ | X | ሀ | ለ | X | X | 0 | 2 | 2 | 0 |

የሦስትዮሽ መፋለስ

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ለ | ሐ | X | መ | ሠ | ረ | X | 3 | 4 | 4 | 1 |
| X | ሀ | ለ | ሐ | X | መ | ሠ | ረ | 0 | 4 | 4 | 0 |
| X | X | ሀ | ለ | ሐ | X | X | X | 0 | 2 | 2 | 0 |
| X | X | X | ሀ | ለ | ሐ | X | X | 0 | 2 | 2 | 0 |
| መ | ሠ | ረ | X | ሀ | ለ | ሐ | X | 0 | 4 | 4 | 0 |

በሠንጠረዥ 4 በቀረበው አሠራር መሠረት የ250 ተማሪዎችን ውጤት ለማስላት 10 ሰከንድ ሊወስድ እንደሚችል አልደርሰንና ሌሎች (2000) ያስረዳሉ፡፡ ስሌቱም የሚከተሉትን አራት ፈርጆች መሠረት ያደርጋል፤

1. ትክክለኛ (exact match)፤ ትክክለኛ ቦታውን ለያዘ ለእያዳንዱ መልስ 1 ነጥብ መመዝገብን ይመለከታል፤
2. ቀዳሚ (previous)፤ በቅደምተከተሉ በማንኛውም ቦታ ትክክለኛ አላባ ላስቀደመ ለእያዳንዱ መልስ 1 ነጥብ መመዝግብን ይመለካታል፤
3. ተከታይ (next)፤ በቅደምተከተሉ በማንኛውም ቦታ ትክክለኛ አላባ ላስከተለ ለእያንዳንዱ መልስ 1 ነጥብ መመዝገብን ይመለከታል፤
4. ዳረኞች (edgs)፤ በመነሻ ወይም በመነሻና በመድረሻ ቦታዎች ትክክለኛ ቦታቸውን ለያዙ መልሶች 1+1 ነጥብ መመዝገብን ይመለከታል፤ ይህም ማለት የመነሻው አላባ ዳረኛ ስለሆነ የሚያስቀድመው ትክክለኛ መልስ አይኖርም፤ መድረሻውም እንዲሁ ዳረኛ በመሆኑ የሚያስከትለው ትክክለኛ መልስ የለውም ማለት ነው፡፡ ይህ አስተራረም ተግባራዊ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት በሦስትዮሽ ሕግ መሠረት የእያንዳንዱ ምላሽ ከፍተኛ ነጥብ 3 ስለሆነ ነው፡፡

በሠንጠረዥ 4 እንደተመለከተው ሦስትዮሽ የውጤት አሰጣጥ ሕግ ከትክክለኛ ቅደምተከተል ውጭ ለከፊል ቅደምተከተል ምላሽ ዋጋ ይሰጣል:: ከዚሁ ጋራ በተያያዘ ግን፣ ተገቢ መልስ የሚሹ ጥያቄዎች የዘዴው ፋይዳ ወይም ጠቀሜታ ምን ያህል ነው? ከሌሎች ዘዴዎች በተለየ

የሚጨምረው ዕሴት ምን ያህል ነው? ትክክለኛነትንና አስተማማኝነትን በምን ያህል ደረጃ ይጨምራል? የሚሉት ናቸው (ኦልደርሰንና ሌሎች፣ 2000)፡፡

የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ ከላይ እንደተገለፀው የራሱ ጥንካሬዎችና ድክመቶች ቢኖሩትም በስፋት የተጠና ጉዳይ ግን አይደለም (ኦልደርሰንና ሌሎች፣ 2000)፡፡ የጥናቱ አስፈላጊነትም ጥያቄውን በአግባቡ በመጠቀም የሚፈለገውን የቋንቋ ክሂል ችሎታ በትክክል ለመለካት እንዲቻል ነው፡፡ ይህም በዐማርኛ ቋንቋ በትምህርትቤት ደረጃም ሆነ በብሔራዊ ወይም በክልል ደረጃ በሚዘጋጁት ፈተናዎች የሚዘወተረውን የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ ለመገምገም መነሻ ኾኗል፡፡ በዋናነትም በጥናቱ በኢትዮጵያ አጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የዐማርኛ ቋንቋ ፈተና ላይ በማተኮር የሚከተሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች ተመርምረዋል፤

በኢትዮጵያ አጠቃላይ ኹለተኛ ደራጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የዐማርኛ ቋንቋ ፈተና፤

1. በቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄና በሚለካው ክሂል ችሎታ መካከል ምን ያህል መጣጣም አለ?
2. ለቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ የሚመረጡ ቴክስቶች ተገቢ የቅደምተከተል አመላካች (አያያዥ) አካላትን በማካተት ረገድ ምን ያህል የተሟሉ ናቸው?
3. የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች ክብደታቸውን የሚመጥን ዋጋ (ነጥብ) አላቸው?
4. የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች በአጠያየቃቸው ምን ያህል ነፃና ራሳቸውን የቻሉ ናቸው?

## የአጠናን ዘዴ

ቀደምሲል እንደተገለፀው የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ በኢትዮጵያ አጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የዐማርኛ ቋንቋ ፈተና የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎችን መገምገም ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ገምጋሚ ስልትን ተከትሎ የተከናወነ ሲሆን፣ ለጥያቄዎቹ የተመረጡትን ቴክስቶች ተገቢ የቅደምተከተል አመላካቾችን በማካተት ረገድ ምን ያህል የተሟሉ እንደሆኑ ይገመግማል፡፡ በተጨማሪም፣ ጥናቱ በቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎችና በሚለኩት የቋንቋ ክሂል ችሎታ መካከል ያለውንም መጣጣም ይገመግማል፡፡ የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች ክብደታቸውን የሚመጥን ዋጋ (ነጥብ) መያዛቸውንም ጥናቱ በተጨማሪ ይገመግማል:: ከዚህም ሌላ የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች የአጠያየቅ ዓይነትና ተገቢነት ተገምግሟል፡፡ በኹሉም ረገድ የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች ግምገማ የተከናወነው በተመራማሪው ሲሆን፣ የእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ ከአሻሚነት ምን ያህል ነፃ እንደሆነ ለማረጋገጥም በመስኩ የሚሠሩ ሦስት የዩኒቨርሲቲ መምህራን በየግላቸው ለጥያቄዎቹ መልስ እንዲጽፉና ስለክብደትና ቅለታቸውም አስተያየት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ ይህም ለግምገማው በግብዓትነት አገልግሏል፡፡

### የጥናቱ መረጃዎችና የመረጃ ምንጮች

ጥናቱ በዋናነት በኢትዮጵያ አጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የዐማርኛ ቋንቋ ፈተና የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የመረጃ ምንጮቹም የአጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የዐማርኛ ፈተናዎች ናቸው፡፡ ከፈተናዎቹ የተወሰዱትም የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች የጥናቱ መረጃዎች ናቸው፡፡ ለዚህም ከ1998-2004 ዓ.ም. ድረስ ያሉት የሰባት ዓመት ፈተናዎች በምክንያታዊ ንሞና ተመርጠዋል፡፡ ዋናው ምክንያትም የሰባቱ ዓመታት ኹሉም ፈተናዎች ቢያንስ አንድ የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ ማካተታቸው ስለተረጋገጠ ነው፡፡ ሠንጠረዥ 5 የጥናቱን የመረጃ ምንጭና መረጃ በዝርዝር ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ 5፤ *የጥናቱ የመረጃ ምንጭና መረጃዎች ዝርዝር መግለጫ*

| ተ.ቁ | ዓ.ም | የጥራዝ መለያ | ብዛት | | አጠያየቅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | የዓረፍተነገር | የጥያቄ | |
| 1. | 2004 | 84 | 4 | 1 | ቅደምተከተል አስተካክል |
| 2. | 2003 | 83 | 7 | 1 | ቅደምተከተል አስተካክል |
| 3. | $2002_{ሀ}$ | 83 | 4 | 1 | ቅደምተከተል አስተካክል |
| | $2002_{ለ}$ | 83 | 4 | 1 | ቅደምተከተል አስተካክል |
| 4. | 2001 | 84 | 4 | 1 | ቅደምተከተል አስተካክል |
| 5. | 2000 | 84 | 4 | 1 | ቅደምተከተል አስተካክል |
| 6. | 1999 | 83 | 5 | 4 | • ቅደምተከተል አስተካክል<br>• የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልት ላይ<br>• መንደርደሪያ ዓረፍተነገር ላይ<br>• የአንቀጽ ቅርጽ ላይ |
| 7. | 1998 | 81 | 4 | 3 | • ቅደምተከተል አስተካክል<br>• ኃይለቃል ላይ<br>• የአንቀጽ ቅርፅ ላይ |

በሰንጠረዥ 5 በተመለከተው መሠረት ከኹሉም ከሰባቱ ዓመት ፈተናዎች የተገኙት ኹሉም የቅደምተከተል አስተካክል ናሙና ጥያቄዎች ለጥናቱ ተመርጠዋል፡፡ ኹሉንም በመረጃነት ማካተት ያስፈለገበት ዋና ምክንያትም ርስበርስ ለማነፃፀርና ግምገማውንም ይበልጥ አስተማማኝ ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ከ2002 ዓ.ም ፈተና ኹለት ራሳቸውን የቻሉ ጥያቄዎችና ከሌሎቹ ዓመታት የተገኙት አንዳንድ ጥያቄዎች በአጠቃላይ ስምንት የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች በናሙናነት ተወስደዋል፡፡

**የመረጃ አተናተን**

የጥናቱ ዓላማ በአጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የዐማርኛ ፈተና የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎችን መገምገም ነው፡፡ ይህንንም ለማሳካት ናሙና ጥያቄዎች ከሰባት ዓመት ፈተናዎች (1998-2004 ዓ.ም.) በቀጥታ ተወስደው ተገምግመዋል፡፡ የመረጃ አተናተኑ ለጥያቄዎቹ የተመረጡትን ቅደምተከተላቸው የተዘበራረቀ ዓረፍተነገሮች በጥልቀት በማስተዋልና በመመርመር ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ለትንተና እንዲያመችም ጥያቄዎቹ መለያ ቁጥር ተሰጥቷቸው በዚሁ መሠረት በቀጥታ እየተጣቀሱ ተገምግመዋል፡፡ በተጨማሪም፣ የመልስ አሻሚነታቸውን ለማወቅ እንዲረዳም አስቀድሞ ስምንቱ ዋና ዋና ጥያቄዎችና በሥራቸው ያካተቷቸው ንዑሳን ጥያቄዎች ይዘታቸውና ቅርፃቸው ሳይቀየር በመስኩ ለሚሠሩ ለሦስት የዩኒቨርሲቲ መምህራን ተሰጥተው መልሳቸው እንዲወሰን ተደርጓል፡፡ በመልስ አወሳሰን ረገድም በሦስቱ መምህራን መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት አልታየም፡፡ በተጨማሪም ሦስቱም መምህራን በሰጧቸው አስተያየቶች የብዙዎቹን ጥያቄዎች አሻሚነትና አስቸጋሪነት ብሎም ውስብስብነት በተጓዳኝ ተጋርተዋል፡፡

የተመረጡትን ናሙና የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎችና ቴክስቶቹን መሠረት በማድረግም ጥያቄዎቹ የትኛውን የዐማርኛ ቋንቋ ክሂል ችሎታ ለመለካት ታስበው እንደተዘጋጁ ለማወቅ በፈተናዎቹ ጥያቄዎቹ የሚገኙበት ንዑስ ክፍል ተመርምሯል፡፡

## የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

ለጥናቱ የተመረጡት መረጃዎች በአግባቡ ከተደራጁ በኋላ ከጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች አንፃር እየተተነተኑ ውጤታቸውም ተብራርቷል፡፡ በግምገማውም አስቀድሞ ኹሉም ጥያቄዎች በሚጋሯቸው እውነታዎች ላይ ነው ለማተኮር የተሞከረው፡፡ በዚህም ስምንቱም ጥያቄዎች አራት አማራጮችን ይዘው በምርጫ ቅርፅ የቀረቡ መሆናቸውንና ለየትኛውም ጥያቄ አንድም መነሻ መልስ (ፍንጭ ጠቋሚ) እንደሌለ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም ጥያቄዎቹን ይበልጥ ውስብስብ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በሠንጠረዥ 6 የተጣቀሰው ናሙና ጥያቄ 05 አንድ መነሻ መልስ ይዞ ቢቀርብ ኖሮ፣ ዓረፍተነገሮቹን በአንድ ብቸኛ ቅደምተከተል ለማደራጀት የሚያጋጥሙትን የአሻሚነት ችግሮች መቀነስ ይቻል ነበር፡፡

*ሠንጠረዥ 6፣ ናሙና ጥያቄ 05*

61. ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የተቀመጡት ዓረፍተነገሮች አንቀጽ እንዲመሠርቱ የሚያስችላቸው የትኛው ቅደምተከተል ነው?

1. ለማንኛውም ብዙ አወጋን፣ ብዙ አጫወተችኝ፣ ታሪኳ በጣም አሳዘነኝ፡፡
2. ትርጉሙን ከዚህ አግኝው ማለቷ ይሆን?
3. መልስ ከመስጠቷ በፊት አካባቢውን በገጿ ፈገግታ ሞላቸው፡፡
4. "ፀዳል ማለት ትርጉሙ ምንድን ነው?" ስል ጠየኳት፡፡

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| A. 3 | 2 | 4 | 1 | C. | 1 | 2 | 3 | 4 |
| B. 2 | 3 | 4 | 1 | ***D.*** | ***4*** | ***3*** | ***2*** | ***1*** |

(ሀ.አ.ት.ም.ፈ.ድ. 2002 (መለያ ጥ.ቁ. 83)፣19/22)

ከሰንጠረዥ 6 መረዳት እንደሚቻለው በናሙና ጥያቄ **05** ሥር ያሉትን አራት ዓረፍተነገሮች ከመጀመሪያው ዓረፍተነገር ጋራ በተያያዘ በአንድ ብቸኛ ቅደምተከተል ለማደራጀት ፈታኝ ነው፡ ፡ በርግጥ ለጥያቄዎቹ መልስ ያዘጋጁት ሦስቱ መምህራን ያለምንም ልዩነት ያመላከቱት ቅደምተከተል [**4፣ 3፣ 2፣ 1]** የሚለውን ነው፡፡ ሌሎቹ አራተኛው፣ ሦስተኛውና ኹለተኛው ዓረፍተነገሮች ምክንታዊ ወይም ተጠየቃዊ ግንኙነት ስላላቸው በዚሁ ቅደምተከተል ሊደራጁ ይችላሉ:: ስለአንደኛው ዓረፍተነገር (1) ግን በቅደምተከተሉ የመድረሻ ወይም የመነሻ ቦታ ብቻ ሊይዝ ስለመቻሉ ምክንያታዊ ማስረጃ ማቅረብ የሚቻል አይመስልም፡፡

በአስተራረም ረገድም የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች ከውስብስብነታቸው ጋራ ተመጣጣኝ የሆነ የተለየ ነጥብ እንዳላቸው የሚያስረዳ መረጃ ከሰባቱም ዓመት ፈተናዎች አልተገኘም፡፡ በኹሉም የፈተና ጥራዞች የውጭ ሽፋን ላይ 90 ጥያቄዎች ስለመካተታቸው የሚገልፅ መረጃ ቢኖርም፣ ስለእያንዳንዱ ጥያቄ ዋጋ (ነጥብ) ግን በየትኛዎቹም የፈተናው ክፍሎች አልተገለፀም፡፡ በጥያቄ አመላለስ ረገድም ከፊል መልስ ስለመፈቀዱ የሚገልፅ መረጃ የለም፡፡ ከዚህም የተለየ ምስጢር ከሌለ በስተቀር፣ የሚጠበቀው ሙሉ መልስ ሆኖ የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች ከሌሎች ጥያቄዎች ጋራ እኩል ዋጋ አላቸው፤ በሚል

መገምት ወይም መላ መምታት የሚቻል ይመስላል፡፡ መላ ምቱም ትክክል ከሆነ በፈተናው የነጥብ አሰጣጡ ፍትሐዊነት የጎደለው መሆኑን ያመላክታል:: ተመጣጣኝ ክብደት ለሌላቸው ጥያቄዎች ተመሳሳይ ውጤት መስጠትና በመጠኑ የሞከሩትን፣ ወደሙሉው መልስ የተቃረቡትንና ሙሉ በሙሉ የተሳሳቱትን ተፈታኞች በእኩል ዓይን መፈረጅ ፍትሐዊ አለመሆኑን ኦልደርሰንና ሌሎች (2000) ይስማማሉ፡፡

በጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች መሠረት በቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎችና በሚለኩት ክሂል ችሎታ መካከል ያለው መጣጣም በተመሳሳይ ሁኔታ አስቀድሞ ተመርምሯል፡፡ ከጥናቱ የመረጃ ምንጭ ፈተናዎች ንባብ ለመረዳት እንደተቻለውም የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎችን በተመለከተ ኹሉም የሰባቱ ዓመት ፈተናዎች ከስምንት እስከዘጠኝ የሚደርሱ ንዑሳን መመሪያዎችንና በሥራቸውም እኩል ባልኾነ መጠን በርከት ያሉ ጥያቄዎችን ቢያካትቱም በጥያቄዎቹ ሊለካ ስለተፈለገው የቋንቋ ክሂል ችሎታና ስለእያንዳንዱ ጥያቄ ዋጋ (ነጥብ) የሚሰጡት መረጃ የለም፡፡

ባችማንና ፓልመር (1996) እንደገለፁት፣ ማንኛውም የፈተና መመሪያ በውስጡ የጥያቄዎቹን (የፈተናውን) ዓላማ፣ የሚለካውን የቋንቋ ክሂል ችሎታ ዓይነት፣ የጥያቄዎችን አመላለስ፣ የትክክለኛ ምላሾችን መስፈርቶች ጨምሮ የነጥብ አሰጣጥን በተመለከተ የተሟሉ መረጃዎችን መስጠት አለበት፡፡ ኹሉም የዚህ ጥናት የመረጃ ምንጭ ፈተናዎች የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ መመሪያዎች ግን የጥያቄዎችን ቁጥርና መልስ አሰጣጥን ከመንገር ባለፈ በቂና ጠቃሚ መረጃዎች የሏቸውም፡፡ በዚህም ምክንያት በየመመሪያው ሥር የተካተቱት ጥያቄዎች በየትኛው የቋንቋ ይዘት ላይ አተኩረው እንደተዘጋጁ ለመረዳት የጋራ ይዘታቸውን መለየት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የኾነው የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ በሚገኝበት ንዑስ መመሪያ ሥር ያሉትን ጥያቄዎች በሰባቱም ዓመት ፈተናዎች ርስበርስ ለማነፃፀር ተሞክሯል፡፡ በዚህም ኹሉም በይዘት ደረጃ የሚጋሩት የመጻፍ ክሂልን እንጂ የማንበብ ክሂልን አለመኾኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለዚህም ይመስላል ከሰባቱ የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች በሦስቱ ናሙና ጥያቄዎች (ናሙና ጥያቄ 01፣ 03፣ 07) ቅደምተከተላቸው ተፋልሶ የቀረቡት ዓረፍተነገሮች ይዘታቸው የአንቀጽን ምንነትና አጻጻፍ የሚመለከት ነው፤ እንዲሁም ሦስቱ ጥያቄዎች (ናሙና ጥያቄ 01፣ 02፣ 08) የአጠያየቅ ትኩረታቸው ኃይለቃልንና የአንቀጽ ቅርፅን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በኹሉም ፈተናዎች ቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ በተካተተበት ንዑስ መመሪያ ሥር ያሉት ኹሉም ጥያቄዎች በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ ትኩረታቸው የመጻፍ ክሂል እንጂ የማንበብ ክሂል አይደለም፡፡ ስለሆነም የመስኩ ተመራማሪዎች (ኦልደርሰንና ሌሎች፣ 2000፤ ብራውን፣ 2004፤ ሂተን፣ 1990፤ ሂዩዝ፣ 2003) እንደሚስማሙበት፣ ቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ የሚዘጋጀው የማንበብ ክሂል ችሎታን ወይም አንብቦ መረዳትን ለመለካት ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ አጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የዐማርኛ ቋንቋ ፈተና ግን የመጻፍ ክሂል ችሎታን ለመለካት ታስቦ ነው የቀረበው፤ ይህም ክብደትን በሜትር ለመለካት ከመሞከር ጋራ ተለይቶ ስለማይታይ ስሕተት መሆኑን ለመረዳት አያስቸግርም፡፡

በኢትዮጵያ አጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የዐማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች የማንበብ ክሂል ችሎታ መለካት ሲኖርባቸው የመጻፍ ክሂል ችሎታን እንዲለኩ ኾነው በመዘጋጀታቸው ምክንያትም መረጃው ከሚችለው ከአንድ ጥያቄ በላይ ያካተቱ አሉ፡፡ ለዚህም አስረጂ እንዲሆን ናሙና ጥያቄ 01 በሠንጠረዥ 7 ቀርቧል፡

**ሠንጠረዥ 7፤** *ናሙና ጥያቄ 01*

*መመሪያ*፣ ከጥያቄ 28 እስከ34 ያሉትን ጥያቄዎች ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች መሠረት በማድረግ መልስ/መልሽ፡፡

1. አንድ ድርሰት ቋንቋው በጣም ያማረ ሆኖ በውስጡ ቁም ነገር ላይኖርበት ይችላል፡፡

2. የድርሰት መሰረት የሐሳብ ፍሬ ነገር ነው፡፡

3. ማንኛውም ድርሰት በውስጡ ፍሬ ነገር ከሌለው ዋጋው ጎደሎ ይሆናል፡፡

4. የቃላት አሰካክ፣ የቋንቋው አጠቃቀም፣ በጠቅላላው የጽሑፉ አቀራረብ ውብ ሆኖ ሳለ፣ ሐሳቡ ፍሬ የሌለው ባዶ ሆኖ ሲገኝ ድርሰቱን ጎደሎ ያደርገዋል፡፡

28. ከዚህ በላይ ተዘበራርቀው የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች በማስተካከል አንቀጽ ሲመሠረት ትክክለኛው የዓረፍተነገር ቅደምተከተል የትኛው ነው?


A. 4፣ 3፣ 2፣ 1 ***C. 2፣3፣1፣4***

B. 2፣ 4፣ 3፣ 1 D. 4፣ 2፣ 1፣ 3

29. የአንቀጹ ኃይለቃል ሊሆን የሚችለው ዓረፍተነገር በተራ ቁጥር ስንት የተገለፀው ነው?

A. 1 B. 2 C. 3 D. 4

30. የአንቀጹ ቅርጽ የትኛውን ሥዕላዊ መግለጫ ይመስላል?




.

(ሀ.አ.ት.ም.ፈ.ድ 1998 (ጥ.ቁ 81)፤ 8-9)

በሠንጠረዥ 7 ከናሙና 01 የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ መመሪያ መረዳት እንደሚቻለው በሥሩ ስድስት ጥያቄዎች መኖራቸውን ቢያመልክትም ከ31 እስከ34 ያሉት ጥያቄዎች በመመሪያው እንደተገለፀው ቅደምተከተላቸው የተዘበራረቀውን አራት ዓረፍተነገሮች መሠረት አድርገው የቀረቡ አይደሉም፡፡ 31ኛው ጥያቄ ስለዘገባ አዘገጃጀት ትክክል ያልሆነውን፣ 32ኛው *እንደዔሊ፤* ከሚለው አነፃፃሪ ሐረግ ሊመሠረት ስለሚችለው ዓረፍተነገር፣ 33ኛው በአወዳዳሪ አገላለፅ የቀረበን ዓረፍተነገር ስለመለየትና 34ኛው የአንድን ሰው ንግግር በቀጥታ ለመጥቀስ ትክክል ስለሆነው የሥርዐተነጥብ አጠቃቀም፣ የሚጠይቁ በመሆናቸው፣ አራቱም ጥቄዎች በግብዓትነት ከቀረቡት አራት ዓረፍተነገሮች ጋራ ምንም ዓይነት ግንኙነት የላቸውም፡፡ ይህም ከፈተና አዘጋጆች ትኩረት ማነስ ወይም ከአርትኦት ጋራ የተያያዘ ችግር ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡

ከመመሪያው ግድፈት በተጨማሪ ግን ሌሎቹም ከሦስቱ ጥያቄዎች ኹለቱ (28ኛውና 29ኛው) ቢኾኑ ለጥያቄዎቹ ግብዓት እንዲሆኑ ከቀረቡት አራት ዓረፍተነገሮች አቅም በላይ የተጠየቁ ናቸው፡፡ ግብአቱን ሊመጥን የሚችለው 28ኛው ጥያቄ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ኹለቱ ጥያቄዎች ግን የግብዓቱን አቅም የሚፈታተኑ ናቸው፡፡ ከዚህም 29ኛውና 30ኛው ጥያቄ ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ነፃ ጥያቄዎች አይደሉም፡፡ የ28ኛው ጥያቄ መልስ ከእሱ ቀጥሎ በቀረቡት በኹለቱ (በ29ኛውና በ30ኛው) ጥያቄዎች መልሶች ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ አለው፡፡ የዓረፍተነገሮቹ

ቅደምተከተል በትክክል ከተስተካከለ ኃይለቃሉና የአንቀጹ ቅርፅ በቀጥታ የሚታወቁ በመሆናቸው እነዚህኑ ጉዳዮች በሌሎች ጥያቄዎች አከታትሎ መጠየቅ ትርጉም አልባ ነው የሚሆነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ዓረፍተነገሮቹን በቅደምተከተል ማስተካከል አለመቻልም በእሱ ላይ የተመሠረቱትን ኹለት ጥያቄዎች መልስ ያሳጣል፡፡ በሌላ አባባል የ28ኛው ጥያቄ ኹለቱን ተከታታይ ጥያቄዎች በቀላሉ ለመመለስ እንደሚያስችል ኹሉ፣ ቀዳሚውን 28ኛውን ጥያቄ መመለስ አለመቻልም በተከታዮቹ ኹለት ጥያቄዎች ለተጨማሪ ኹለት ስሕተቶች ይዳርጋል ማለት ነው፡፡ ባችማን (1995) እንደገለፁት፣ አንድ የቋንቋ ክሂል ችሎታ ለመለካት የሚዘጋጁ ጥያቄዎች ራሳቸውን ችለው አንድ ነጠላ ችሎታ መለካት አለባቸው፡፡ የአንደኛው ጥያቄ መልስ በሌላው ጥያቄ መልስ ላይ በምንም ሁኔታ ተፅዕኖ ማሳረፍ የለበትም፡፡ ተፈታኞች የቀዳሚውን ጥያቄ መልሰው ወደተከታዩ ጥያቄ በማለፍ መልስ ከሰጡ በኋላ እንደገና ተመልሰው የቀዳሚውን ጥያቄ መልስ የሚለውጡ ሲሆን፣ ወይም ደግሞ የቀዳሚውን ጥያቄ መልስ መሠረት በማድረግ የተከታዩን ጥያቄ ከመለሱ፣ ወይም የቀዳሚው ጥያቄ ስሕተት መልስ በተከታዩ ጥያቄ ለሌላ ስሕተት የሚዳርግ ከሆነ፣ እነዚህ ጥያቄዎች ራሳቸውን ችለው አንድን ነጠላ ችሎታ ለመለካት የሚችሉ አለመሆናቸውን ያመላክታል፡፡ የእያዳንዱ ጥያቄ የክብደት ደረጃም እኩል ተመጣጣኝ እንዲሆን እንጂ አንዱ የሌላው ጥገኛ እንዲሆን አይጠበቅም፡፡ በሠንጠረዥ 7 የቀረበው ናሙና ጥያቄም ከዚህ ከባችማን (1995) እሙን ጋራ የሚጋጭ ስለመሆኑ ለመረዳት አይቸግርም፡፡ ቀደምሲል እንደተገለፀው ዓረፍተነገሮቹ ቅደምተከተላቸው ከተስተካከለ ኃይለቃሉን በቀላሉ ለመለየት ይቻላል፡፡ ይህም በራሱ የአንቀጹን ቅርፅ ቀጥተኛ አመልካች ነው፡፡

የናሙና ጥያቄ 01 ሌላው ችግር ደግሞ ቅደምተከተላቸው የተፋለሰውን ዓረፍተነገሮች በአንድ ብቸኛ ቅደምተከተል ለማደራጀት የግድ የሚያደርጉ ቅደምተከተል አመላካች አካላት አለመኖራቸው ነው፡፡ በርግጥ በዚህ ጥናት ለጥያቄዎቹ መልስ እንዲያዘጋጁ የተጠየቁት ሦስቱ መምህራን (ኹለቱ አሻሚነቱን በመጠቆም ጭምር) ያለልዩነት ያመላከቱት ቅደምተከተል [2፣ 3፣ 1፣ 4] በሚል ነው፡፡ ነገርግን በአራቱም ዓረፍተነገሮች ተደጋጋሚ ቃላት ቢኖሩም በመምህራኑ የተመለከተውን ቅደምተከተል የግድ የሚያደርጉ ወይም የትኛው ሐሳብ ቀድሞ የትኛው መከተል እንዳለበት የሚያመላክቱ ጠቋሚ አያያዞች የሉም፡፡ የዓረፍተነገሮቹን ሐሳቦች በጥቅልና በዝርዝር ግንኙነት ለማደራጀት ቢሞከርም 2ኛውና 3ኛው፣ 1ኛውና 4ኛው ዓረፍተነገሮች እጅግ ሲበዛ አሻሚዎች ናቸው፡፡ ስለዚህም አራቱን ዓረፍተነገሮች በአንድ ብቸኛ ቅደምተከተል ለማደራጀት የሚቻል አይመስልም፡፡ የዚህም ችግር ከ28ኛው ጥያቄ አልፎ ያለምክንያት ለተካተቱት ለ29ኛውና ለ30ኛው ጥያቄዎች እንደሚተርፍ በጣም ግልፅ ነው፡፡

በሠንጠረዥ 8 የቀረበው ናሙና ጥያቄ 02፣ ከናሙና ጥያቄ 01 ጋራ የሚጋሯቸው ችግሮች እንዳሉ ኹሉ የራሱ ጥንካሬዎችም አሉት፡፡ ዓረፍተነገሮቹ ተገቢ ቅደምተከተል አመላካቾች መያዛቸው የናሙና ጥያቄ 02 ጥንካሬ ነው፡፡ ለጥያቄዎቹ መልስ ያዘጋጁት መምህራን ያለልዩነት [ለ፣ መ፣ ሀ፣ ሐ፣ ሠ] በሚል ያመላከቱት ቅደምተከተል ምክንያታዊ ይመስላል፡፡ በትክክለኛ ቅደምተከተላቸው ከሌሎቹ ዓረፍተነገሮች አንፃር ሲታይ የተጠቃለለ ሐሳብ በመያዙ ኹለተኛው ዓረፍተነገር (ለ) መነሻ እንዲሆን ግድ ነው:: በመቀጠልም በመጀመሪያው ዓረፍተነገር ለተጠቀሰው ሐሳብ በተቃርኗዊ ምክንያት አስረጂ ስለሚሰጥ አራተኛው ዓረፍተነገር (መ) ኹለተኛውን ቦታ ይይዛል:: በዚህ በኹለተኛው ዓረፍተነገር ለቀረበው አስረጂ ተጨማሪ ምክንያት የሚሰጠው ደግሞ አንደኛው ዓረፍተነገር (ሀ) ስለሆነ ሦስተኛውን ቦታ ይይዛል:: በዓረፍተነገሩ መነሻ ላይ ያለው ጠቋሚ/አመልካች መስተአምር (ከዚህ የተነሳ) የሁለቱን ዓረፍተነገሮች ክትትሎሽ በጣም ምክንያታዊ ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም ሌላ አመልካች መስተአምር ያለው ሦስተኛው ዓረፍተነገር (ሐ) የአራተኛውን ዓረፍተነገር አንድምታ

ስለሚያሳይና ዐምስተኛው ዓረፍተነገር ደግሞ የአንቀጹ መደምደሚያ በመሆኑ በቅደምተከተሉ አራተኛና ዐምስተኛ ቦታ ይይዛሉ፡፡

***ሠንጠረዥ 8፤*** *ናሙና ጥያቄ 02*

***መመሪያ፤*** ከሀ-ሠ የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች በማስተዋል፣ ከተራ ቁጥር 24 እስከ27 ድረስ ላሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን ምረጭ/ምረጥ፡፡

ሀ. ከዚህ የተነሳ የዘር ውርስ 30 በመቶ፣ የአካባቢ ተፅዕኖ ደግሞ 70 በመቶ ድርሻ አላቸው፡፡

ለ. በዘር እና ከአካባቢ የሚወረሱ ጉዳዮች ለአእምሮ መጎልበት አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

ሐ. ይህ የሚያሳየው የአካባቢ ተጽዕኖ ለአእምሮ መጎልበት የጎላ አስተዋጽኦ እንዳለው ነው፡፡

መ. ይሁን እንጅ አብዛኛውን ድርሻ ይይዛል የሚባለው አካባቢያዊ ተጽእኖ ነው፡፡

ሠ. በመሆኑም ልጆች ምቹ አካባቢያዊ ሁኔታ እንዲኖራቸው መጣር ይገባል፡፡

24. ዓረፍተነገሮቹ የተስተካከለ ሐሳብ እንዲያስተላልፉ ተገቢ የሚሆነው የአደራደር ቅደምተከተል የትኛው ነው?

A. መ፣ ሐ፣ ሀ፣ ሠ፣ መ **C. ለ፣ መ፣ ሀ፣ ሐ፣ ሠ**

B. ሐ፣ ለ፣ ሀ፣ ሠ፣ መ D. ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ፣ ሠ


25. ዓረፍተነገሮቹ ቅደምተከተላቸውን ሲጠብቁ የሚመሠረተው አንቀጽ ለየትኛው አንቀጽ ማስፋፊያ ስልት ምሳሌ ይሆናል?


A. ትረካ B. ገለፃ C. መንስኤና ውጤት D. ማወዳደር

26. ለሚመሠረተው አንቀጽ መንደርደሪያ ዓረፍተነገር የትኛው ነው?

A. ለ B. ሀ C. ሐ. D. ሠ

27. የሚመሠረተው አንቀፅ ቅርጽ የትኛውን ሥዕላዊ መግለጫ ይመስላል?

A.  C. 

B.  D. 

(ሀ.አ.ት.ም.ፈ.ድ. 1999 (ጥ.ቁ. 83 )፤7-8)

በቅደምተከተል አመላካች አካላት ረገድ ናሙና ጥያቄ 04 የናሙና ጥያቄ 02ን ጥንካሬ የሚጋራ ኾኖ ተገኝቷል፡፡ ከሠንጠረዥ 9 መረዳት እንደሚቻለው በናሙና ጥያቄ 4 እንደናሙና ጥያቄ 02 ኹሉ፣ ዓረፍተነገሮቹ በአንድ ብቸኛ ቅደምተከተል እንዲዋቀሩ የግድ የሚያደርጉ ተገቢ የሆኑ ቅደምተከተል አመላካቾች አሏቸው፡፡ በቅደምተከተሉ ቀዳሚው ዓረፍተነገር አራተኛው (መ) ሲሆን፣ ኹለተኛ የሚሆነው ደግሞ አንደኛው (ሀ) ነው፤ ይህንንም የግድ የሚያደርጉት በኹለቱ ተከታታይ ዓረፍተነገሮች “ስልጣኔ” የሚለው ተደጋሚ ቃልና ከአራተኛው ዓረፍተነገር ጋራ ሲነፃፀር የኹለተኛው ሐሳብ ዝርዝር መሆኑ ናቸው፡፡ በሦስተኛ ደረጃ የሚከተለው ደግሞ ሦስተኛው ዓረፍተነገር (ሐ) ሲሆን፣ ይህም ከቀዳሚው ዓረፍተነገር ጋራ ያለው ግንኙነት “ምክንያቱም” በሚለው ተጠየቃዊ አመላካች ተጠቁሟል:: ለዚህም ነው የጥያቄዎቹ መልስ

አዘጋጆችም ያለልዩነት [መ፣ ሀ፣ ሐ፣ ለ] በሚል ያመላከቱት ቅደምተከተል ምክንያታዊ ነው ሊባል የሚችለው፡፡

***ሠንጠረዥ 9፤*** *ናሙና ጥያቄ 04*

7. ከዚህ በታች ቅደምተከተላቸው ተዘበራርቆ የተቀመጡት ዓረፍተነገሮች ተቃንተው ቢፃፉ፣ ትክክለኛው ቅደም ተከተላዊ አቀማመጣቸው የትኛው ነው?

*ሀ. ስልጣኔ አንድ ገበሬ መሬቱ አርጅቷል፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሌላ ፈልጌ አርሳለሁ እንዲል አይፈቅድለትም፡፡*

*ለ. ከዚህ በተጨማሪም ስልጣኔ ለርቢና ለፍራፍሬ የሚሆኑትን እየለየ በያግባባቸው እያሻሻለ የሚጠቀምበትን ብልሀት ይጠቁመዋል፡፡*

*ሐ. ምክንያቱም መሬቱ ፍግና ልዩ ልዩ ማዕድናት በመመገብ እንደሚታደስ ስለሚያስተምረው ነው፡፡*

*መ. ስልጣኔ እንኩዋን በከተማ ይቅርና በገጠርም ቢሆን ህዝቡ የእርሻውን ዘዴ እያሻሻለ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡*

A. *መ፣ ሐ፣ ለ፣ ሐ* **C. *መ፣ ሀ፣ ሐ፣ ለ***

B. *ለ፣ ሀ፣ ሐ፣ መ* D. *ለ፣ ሐ፣ ሀ፣ መ*

(*ሀ.ኢ.ት.ም.ፈ.ድ.* 2001፣ *ጥ.ቁ* 84)፤3-4)

ናሙና ጥያቄ 02 በሠንጠረዥ 9 ከቀረበው ከናሙና ጥያቄ 04 ጋራ የሚጋራቸው ጥንካሬዎች ቢኖሩትም ከችግር ነፃ ነው ማለት ግን አይደለም፡፡ ከጥንካሬዎቹ ባሻገር ናሙና ጥያቄ 02 ከናሙና ጥያቄ 01 ጋራ የሚጋራቸው ችግሮችም አሉት፡፡ በተለይም 26ኛውና 27ኛው ጥያቄ ራሳቸውን ችለው አንድን ነጠላ የቋንቋ ችሎታ የሚለኩ ነፃ ጥያቄዎች አይደሉም፡፡ ዓረፍተነገሮቹን በትክክለኛው ቅደምተከተል ማደራጀት መቻል በራሱ የአንቀጹን መንደርደሪያ ዓረፍተነገርና ሥዕላዊ ቅርፁን ለመለየት ያስችላል፡፡ ስለሆነም 24ኛው፣ 26ኛውና 27ኛው ጥያቄዎች ርስበርስ መረጃ የሚመጋገቡ በመሆናቸው ኹለቱም (26ኛውና 27ኛው) ያለምክንያት የቀረቡ ትርፍ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

ከላይ እንደቀረቡት ናሙና ጥያቄዎች 01 እና 02 በግልፅ የተመለከተ ባይሆንም፣ ናሙና ጥያቄ 08 አላስፈላጊ ጥያቄን በመያዙ የኹለቱን [01 እና 02]፣ የቅደምተከተል አመላካቾችን ባለማካተቱ የናሙና ጥያቄን 01 ችግሮች ይጋራል፡፡ ከሠንጠረዥ 10 መረዳት እንደሚቻለው ናሙና ጥያቄ 08 በአንድ ጥያቄ ኹለት ተግባራት መሥራትን ይጠይቃል፤ በቀጥታ የተጠየቀው ኃይለቃሉን መለየት ቢሆንም እሱን ለመለየትም ዓረፍተነገሮቹን በቅደምተከተል ማደራጀትን መመሪያው ግድ ያደርጋል፡፡ ለዚህም አስቀድሞ ዓረፍተነገሮቹን በቅደምተከተል ማደራጀት ያስፈልጋል:: ይህም በትክክል ከተከናወነ ኃይለቃሉን መለየት ተጨማሪ ሥራ የሚጠይቅ አይሆንም፡፡ ተጨማሪ ሥራ ወይም ጥረት የማይጠይቀው የዓረፍተነገሮቹ ቅደምተከተል ሳይፋለስ ቢቀርብ ነበር፡፡ ተጨማሪ ሥራ የማይጠይቅ ጥያቄ ደግሞ ራሱን ችሎ የተለየ ችሎታን ሊለካ አይችልም:: በመሆኑም፣ ዓረፍተነገሮቹን በቅደምተከተል ከማደራጀት ባለፈ ኃይለቃል መለየትን በተመለከተ የቀረበው ጥያቄ ተገቢ ነው ሊባል አይችልም፡፡

***ሠንጠረዥ 10፤*** *ናሙና ጥያቄ 08*

41. ቅደምተከተላቸው የተዘበራረቀው የሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ተቃንተው የሚመሠርቱት አንቀጽ ኃይለቃል ሊሆን የሚገባው የትኛው ነው?

*ሀ. እንደሀር ነዶ እየተዘናፈለ ወርዶ ዳሌዋን የሚዳስሰው ፀጉሯ የውበቷ ሰገነት ነው፡፡*

ለ. መልከትከት ስታደርግ እንደፈርጥ ይንቦገቦጋል፡፡

ሐ. ሰልፍ እንዳማረላቸው ወታደሮች ችምችም ብለው የበቀሉት ጥርሶቿ ሀጫ በረዶ ይመስላል፡፡

መ. ምን ጊዜ በሳቀች የምትባል ዓይነት ነች፡፡

ሠ. ሽፋሽፍቷ እንደበልግ ሳር ተጨብጦ የሚታጨድ ይመስላል፡፡

***ረ. ትዕግስት በአሰራዎቹ እድሜ ላይ የምትገኝ ለግላጋ ውብ ወጣት ናት፡፡***

ሰ. ዓይኗ ከብር አሎሎ ይፎካከራል፡፡

A. ምን ጊዜ በሳቀች የምትባል አይነት ነች፡፡

B. አይኗ ከብር አሎሎ ይፎካከራል፡፡

C. እንደሀር ነዶ እየተዘናፈለ ወርዶ ሂዶ ዳሌዋን የሚዳስሰው ፀጉሯ የውበቷ ሰገነት ነው፡፡

D. ትግስት በአሰራዎቹ እድሜ ላይ የምትገኝ ለግላጋ ውብ ወጣት ናት፡፡

(ሀ.አ.ት.ም.ፈ.ድ. 2003 (መለያ ጥ.ቁ. 83)፤12)

ከዚህም ሌላ በናሙና ጥያቄ 02 በግብዓትነት የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች በአንድ ብቸኛ ቅደምተከተል ለማዋቀር የሚያግዙ ቅደምተከተል አመላካች አካላት (አያያዦች) የሉም፡፡ ምናልባትም ከዓረፍተነገሮቹ ይዘት መገመት እንደሚቻለው ለቅደምተከተል ማደራጃ ታሳቢ የሆነው አቅጣጫ (ሐሳብን ከላይ ወደታች ማደራጀት) ነው፤ ሊባል ይችላል፡፡ በዚህ ጥናት ለጥያቄዎቹ መልስ ያዘጋጁት ሦስቱ መምህራንም በዚህ መነሻ ይመስላል ኃይለቃል እንዲሆን የለዩት ስድስተኛውን ዓረፍተነገር (ረ) ነው፡፡ ዓረፍተነገሩ ኃይለቃል ስለመሆኑ የሚያከራክር ባይሆንም ቦታውንና ተከታዩን ዓረፍተነገር በሚመለከት ግን አሻሚነት አለ፡፡ ዓረፍተነገሮቹ በቅደምተከተል ሲደራጁ መነሻ የሚሆነው ስድስተኛው (ረ) ዓረፍተነገር ቢሆን ለምሳሌ፣ በአንድ ቦታ ከእሱ ቀጥሎ ሊመጡ የሚችሉ ቢያንስ ኹለት ዓረፍተነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የዓረፍተነገሮቹ ትኩረት ስለትዕግሥት አካላዊ ውበት ሲሆን፣ ይህንንም ለመግለፅ በአንድ አማራጭ በቀረበው መረጃ መሠረት ከላይ ከራስ በመጀመር ዓይን፣ ጥርስ እያሉ መውረድ ሲቻል፣ በሌላ አማራጭ ደግሞ ከታች ከጥርስ በመነሳት ዓይን፣ ፀጉር እያሉ ወደላይ መዝለቅ፣ ከኹለቱ አንደኛውን በመከተልም በርዕሱ ባለጉዳይ **በትዕግሥት** ለመጀመር ወይም ለመደምደም የሚከለክል ነገርም የለም፡፡ ስለሆነም እንደዚህ አማራጮቹ ብዙ ሆነው እያለ የሚጠበቀውን አንድ ብቸኛ ቅደምተከተል ፍትሐዊ አያደርገውም፡፡

ባጠቃላይ፣ ከላይ በዝርዝር እንደቀረበው ናሙና ጥያቄዎችንና ግብዓቶቻቸውን መሠረት በማድረግ የጥናቱን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ተሞክሯል፡፡ ኹሉም የቅደምተከተል አስተካክል ናሙና ጥያቄዎች ከቋንቋ ፈተና መርህ አንፃር መለካት ያለባቸውን የቋንቋ ችሎታ ለመለካት ታስበው ያልተዘጋጁ መሆናቸውን የውጤት ትንተናው አመላክቷል፡፡ የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች የማንበብ ክሂል ችሎታን ለመለካት በአግባቡ መዘጋጀት ሲኖርባቸው ከመስመር ውጭ የመፃፍ ክሂል ችሎታን ለመመዘን ታስበው መቅረባቸው ትክክለኛነታቸውን ጥያቄ ውስጥ አስገብቶታል፡፡ በጥያቄዎች መካከል ያለው መደጋገፍም ሌላው ችግራቸው መሆኑን የውጤት ትንተናው አመላክቷል፡፡ በተጨማሪም፣ የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች ውሰብስብነታቸውን ለማካካስ የሚያስችሉ ቢያንስ አንድ መነሻ መልስ ይዘው አለመዘጋጀታቸውን ከውጤት ትንተናው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአስተራረም ረገድም የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች በባሕርያቸው ውስብስብና ሰፊ ጊዜ የሚጠይቁ ሆነው እያለ ከሌሎች ጥያቄዎች ጋራ እኩል ዋጋ መያዛቸው ፍትሐዊ አለመሆኑን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ በብዙዎቹ የቅደምተከል አስተካክል ጥያቄዎች በግብዓትነት በቀረቡት ዓረፍተነገሮች

ተገቢ የቅደምተከተል አመላካቾች አለመኖራቸውም የጥያቄዎቹን ውስብስብነት ብሎም አስቸጋሪነት እንደሚጨምረው ለመረዳት ተችሏል፡፡

## ማጠቃለያ

ከመነሻው እንደተገለፀው የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ በኢትዮጵያ አጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የዐማርኛ ቋንቋ ፈተና የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎችን መገምገም ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ጥናቱ የተከተለው የግምገማ ስልትን ሲሆን፣ ለዚህም የሰባት ዓመት ፈተናዎች በዓላማ ንሞና ተመርጠው የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች ከጥናቱ ትኩረቶች አንፃር ተገምግመዋል፡፡ ዋና ዋና የግምገማ ነጥቦችም ጥያቄዎቹ በሚለኩት የቋንቋ ችሎታ፣ በቅደምተከተል አመላካቾች፣ በመነሻ መልስ፣ በነጥብ አሰጣጥና በጥያቄዎች ብቸኛነት (ነፃነት) ላያ ያተኩሩ ናቸው፡፡

የጥናቱ ውጤት እንዳመለከተው በኢትዮጵያ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የዐማርኛ ቋንቋ ፈተና የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች መለካት ያለባቸውን የቋንቋ ክሂል ችሎታ እንዲለኩ ኾነው የቀረቡ አይደሉም፡፡ የመስኩ ባለሙያዎች እንደሚስማሙበት የዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ምድባቸው ከማንበብ ክሂል ችሎታ መመዘኛ ጥያቄዎች ጋራ እንጂ ከመጻፍ ክሂል ችሎታ መመዘኛ ጥያቄዎች ጋራ አይደለም፡፡ ከዚህም ሌላ ከኹለት ጥያቄዎች በስተቀር (ናሙና ጥያቄ 02 እና 04) በሌሎቹ ዐምስት ጥያቄዎች ቅደምተከተላቸው የተፋለሰው ዓረፍተነገሮች በአንድ ብቸኛ ቅደምተከተል ለማደራጀት የሚያስችሉ ተገቢ ቅደምተከተል አመላካቾች የሏቸውም፡፡ በተጨማሪም፣ ጥያቄዎቹ ቢያንስ አንድ መነሻ መልስ ይዘው አለመቅረባቸው ይበልጥ ውስብስብ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ ይሁንእንጂ ቢያንስ ከውስብስብነታቸው ጋራ የሚጣጣም ዋጋ ሊኖራቸው ሲገባ የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች ነጥብ፣ ከሌሎች ጥያቄዎች ጋራ እኩል መሆኑን የውጤት ትንተናው አሳይቷል፡፡ ጥያቄዎቹ ከዚህም ሌላ ከውስብስብነታቸው የተነሳ ከፊል መልስ የማይፈቅዱ በመሆናቸው የፍትሐዊነት ችግር እንዳለባቸው ከውጤት ትንተናው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአጠያየቅ ረገድም በተለይም ኹለቱ የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች (ናሙና ጥያቄ 01 እና 02) ራሳቸውን ችለው አንድን የቋንቋ ችሎታ የማይለኩ አንደኛው የሌላው ጥገኛ የሆኑ ጥያቄዎች ይዘው ተገኝተዋል፡፡ በጥናቱ ውጤት መሠረት ከቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች ጋራ የተያያዙ ችግሮችን በመጠኑም ቢሆን መቀነስ ያስችላሉ ተብለው የታሰቡ አስተያየቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

1. በመርህ ደረጃ ማስተማርን ከመፈተን ነጥሎ ማየት ስለማይቻል ፈተናዎች የሥርዐተትምህርቱና የመማር ማስተማሩ ነፀብራቆች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት ውጤት መሠረት ከቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች ጋራ የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት በአንድ አማራጭ የዐማርኛ ቋንቋን ሥርዐተትምህርት ብሎም የመማር ማስተማር ሂደት መፈተሽ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፤

2. የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎችን የማንብብ ክሂል ችሎታን ብቻ መለካት እንዲችሉ አድርገው እንዲያዘጋጁ የፈተና አዘጋጆችን ማሳወቅ/ማሰልጠን ያስፈልጋል፡፡ ይህም የሚያዘጋጁትን የፈተና ጥያቄ ትክክለኛ ተግባር በትክክል ለይተው እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፤

3. የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች ቢያንስ አንድ መነሻ መልስ ይዘው እንዲዘጋጁ ቢደረጉ በመልስ አሰጣጥ ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ አሻሚዎችን መቀነስ ይቻላል፤

4. የቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄዎች ከውስብስብነታቸውና ከሚጠይቁት ሰአት ጋራ የሚመጣጠን ፍትሐዊ ዋጋ (ነጥብ) እንዲኖራቸው ለከፊል መልስ ከፊል ነጥብ መስጠት የሚያስችል በአግባቡ የተጠና ስልት መቀየስ ያስፈልጋል፤

5. ለቅደምተከተል አስተካክል ጥያቄ የሚመረጡትን ውሕድአሀዶች (ቴክስቶች) ዓረፍተነገሮች በአንድ ብቸኛ ቅደምተከተል ለማደራጀት የሚያግዙ ተገቢ ቅደምተከተል አመላካቾች እንዲኖሯቸው አድርጎ ማቅረብ ቢቻል፣ በተፈታኞች ላይ የሚደርሰውን ጫና በመጠኑም ቢሆን መቀነስ ይቻላል፡፡

## ምስጋና

ሰፋ መካ (ፒኤች ዲ)፣ ሰላማዊት ሳፊሳ (ፒኤች ዲ) እና ሰሎሜ ዘውድዓለም (ፒኤች ዲ) የጥናቱን የመረጃ ምንጭ ፈተናዎች የጥያቄዎችን መልስ ለመወሰን ስለተባበሩ፣ ስማችሁ ያልተጠቀሰው የዚህ መጣጥፍ የምስጢር ገምጋሚዎች ስለሙያዊ የማሻሻያ አስተያየቶቻችሁ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

## ዋቢዎች

Alderson, J. C., Clapham, C., & Wall, D. (1995). *Language test construction and evaluation*. Cambridge: Cambridge University Press.

Alderson, J.C., Percsich, R. & Szabo, G. (2000). Sequencing as an item type. *ltj.sagepub.com* at HINARI.

Bachman, L. F. (1995). *Fundamental considerations in language testing*. Oxford: Oxford University Press.

Bachman, L. F. & Palmer, A. (1996). *Language test in practice: Designing and developing useful language tests*. Oxford: Oxford University Press.

Brown, D. H. (2004). *Language assessment principles and classroom practices*. USA: Pearson education, Inc.

Heaton, J. B. (1990). *Writing English language tests* (New Edition). London: Longman, Inc.

Hughes, A. (1992). *Testing for language teachers.* Cambridge: Cambridge university press.

## አባሪ፤ ናሙና ጥያቄዎች

**ናሙና ጥያቄ 03**

5. ከዚህ በታች ቅደም ተከተላቸው ተዘበራርቆ የተፃፉት አረፍተነገሮች ተቃንተው አንቀፅ ቢመሰረት፣ ትክክለኛው የሀሳብ ቅደም ተከተል የትኛው ነው?

1. የአንድ ድርሰት አነስተኛ ክፍልም አንቀጽ ተብሎ ይጠራል፡፡
2. የአንቀጽ አፃፃፍ ልክ እንደዓረፍተነገር ነው፡፡
3. ድርሰት ስንፅፍ በልዩ ልዩ አነስተኛ ክፍል እንከፍለዋለን፡፡
4. ነገር ግን ተገላጩን ነገር አስፋፍቶ ስለሚያስረዳ ጥቂት ከዓረፍተነገር ይለያል፡፡

A. 4 2 1 3 C. 3 1 2 4

***B*. 3 1 2 4**** D. 4 3 2 1

*መልስ (ሀ.አ.ት.ም.ፈ.ድ. 2000 (መለያ 01 )፤2)

**ናሙና ጥያቄ 05**

70. የሚከተሉት ፍሬነገሮች በአቶ ነጋሳ የህይዎት ታሪክ ውስጥ በቅደምተከተል የሚቀርቡት እንዴት ነው?

1. ከጣልያን ወረራ በኋላ ትዳር መስርተው ሁለት ልጆች ከወለዱ በኋላ በ1945 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡

2. በልጅነታቸው ከወላጅ አባታቸው ዲላማ መተኮስንና ሌሎች የጀግንነት ተግባራትን እየተማሩ አደጉ፡፡

3. አቶ ነጋሳ በቀለ ከአባታቸው ከአቶ በቀለ አብዲና ከእናታቸው ከወ/ሮ ቀነኒ ገመዳ በ1908 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ፡፡

4. ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረበት ጊዜ በደቡብ በኩል ከዘምተው ሰራዊት ጋራ አብረው ዘመቱ፡፡

A. 2 4 3 1 C. 3 4 2 1

***B*. 3 2 4 1*** D. 2 3 4 1

*መልስ (ሀ.አ.ት.ም.ፈ.ድ. 2002 (መለያ ጥ.ቁ. 83)፤ 19/22)

**ናሙና ጥያቄ 07**

8. ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የተቀመጡት ዓረፍተነገሮች ተቃንተው ቢፃፉ የዓረፍተነገሩ ቅደምተከተል ምን ይሆናል?

1. ለዚህም በሀይለቃሉና እሱን በሚያብራሩት ዓረፍነተነገሮች መካከል ግልፅ የሆነ ዝምድና መኖር አለበት፡፡

2. አንቀፁን ሙሉ በሙሉ የመቆጣጠር ሀይል አለው፡፡

3. ሀይለቃል በአጠቃላይ መንደርደሪያ ሀሳብ ሲሆን፣ የአንቀፁ አቢይ ጭብጥ በመሆን ያገለግላል፡፡

4. አንድ አንቀፅ በውስጡ ሀይለቃል የሚባል ዋና ክፍል አለው፡፡

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| A. 1 | 2 | 3 | 4 | ***C*. 4*** | ***3*** | ***2*** | ***1*** |
| B. 3 | 2 | 4 | 1 | D. 2 | 3 | 1 | 4 |

*መልስ (ሀ.አ.ት.ም.ፈ.ድ. 2004 (መለያ ፐ.ቁ. 84)፤3)